Hallo
Basel-Stadt

Kanton Basel-Stadt

# ቋንቋና ውህደት

ውህደት
ለመወሃሃድ የሚረዱ አቅርቦቶች
ቋንቋ
ጀርመንኛ ቋንቋ መማር

# ውህደት

በBasel-Stadt ካንቶን የሚኖሩ ከሆነ፣ እንደነዋሪ መጠን የተወሰነ መብት አለዎት። ጾታዎ ወንድ ይሁን ሴት ቢሆን፣ ከየትም አገር ይምጡ፣ የፈለጉትን ቋንቋ ይናገሩ፣ በየትኛውም ሃይማኖት ይመኑ ወይም የሆነ ዓይነት ስንክልና ይኑሮት፣ ምንም ልዩነትና ለውጥ አያመጣም። የአገሪቱን ሕግ ግን የማክበር ግዴታ አለብዎት። ከዚህ በተጨማሪም በኢኮኖሚ ራስዎን መቻል እንዲሁም ጀርመንኛ መማር አለብዎት። ይህንን በሚመለከት ከዚህ በታች በቂ መረጃ ያገኛሉ።

## ጠቃሚ መሰረታዊ ሕጎች

ስዊዘርላንድ ውስጥ የሚኖሩ ከሆነ፣ የፌደራሉን ሕገ መንግስትና እንዲሁም ሌሎች ሕጎችን የግድ ማክበር አለብዎት። ይህ ማለት ለምሳሌ ያህል፣ ሁሉም ሰው በእኩልነት መስተናገድ አለበት፣ ማንም ሰው መገለል የለበትም። የባዝል ነዋሪ ከሆኑ ጀርመንኛ መማር ይገባዎታል። ከዛ በተጨማሪም በኢኮኖሚ ራስህዎን መቻል አለብዎት።
በመግባባት ተዋህዶ መኖር የሚቻለው፣ ሁሉም ሰው ድርሻውን አስተዋጽኦ ሲያደርግ ነው። የባዝል ህዝብ በወገኑ ለእናንተ ክፍት መሆን አለበት። ህዝቡ መረጃ በመስጠት መተባበርና ድጋፍ ማድረግ አለበት።

## የግለሰብ ሃላፊነት

ወደ ባዝል ከተማ አዲስ ነው የመጡት? በኢኮኖሚ፣ በሶሻል እና በባህላዊ ህይወት ውስጥ ተካፋይ እንዲሆኑ ፌደራሉ፣ ካንቶኖች እና ኮምዩኖች ተገቢው ዕድል የመስጠትና የማመቻቸት ሃላፊነት አለባቸው። ሆኖም ግን እርስዎ በአግባቡ ለመወሃሃድ ጥረት ማድረግ አለብዎት። ከርስዎ የምንጠብቀው፣ በአግባቡ ለመወሃሃድ እንዲያግዝ በማለት የተዘጋጁትን የውህደት አቅርቦቶች በትክክል እንዲጠቀሙበት ነው።

## በማህበራዊ ህይወት ውስጥ መሳተፍ

በዚህ መልክ በአግባቡ መዋሃድ ይችላሉ፣ በማህበራት ውስጥ በጣም መልካም ሰዎችን መተዋወቅ ይችላሉ። ወይም በመኖሪያዎ አካባቢ በሚዘጋጁ ማህበራዊ በዓላቶችና ዝግጅቶች መሳተፍ ይረዳል። ምናልባት በመጀመሪያ ግዜ ከባድ ሊሆን ይችላል። አንዳንድ ሰዎች ከሌላ አገር መጤ ከሆኑ ሰዎች ጋር ለመግባባት ክፍት አይደሉም። ይሁን እንጂ ብዙ ሰዎች ለመላመድ ግዜ ያስፈልጋቸዋል፣ ቀስ በቀስ ግን ፈታ እያሉ ይመጣሉ። ስለዚህ በቀላሉ ተስፋ አይቁረጡ።

## መረጃዎች / ድጋፍ

ወደ ባዝል አዲስ ነው የመጡት፣ ስለሆነም ድጋፍና መረጃ ያስፈልግዎታል? በ Basel-Stadt መረጃ ማግኘትና መጠየቅ የሚችሉባቸው የተለያዩ ቦታዎችን ማግኘት ይችላሉ። በ Basel-Stadt ካንቶን አስተዳደር ጽ/ቤቶች እና በሚኖሩበት ኮምዩን ጽ/ቤት መረጃዎች ማግኘት ይችላሉ። ይሁን እንጂ ለስደተኞች የተለየ የመረጃ መስጫ አገልግሎት ቢሮዎች አሉ።
በስዊዘርላንድ ስላለው ሕይወት እና ስለ ሌሎች ርዕሰ ጉዳዮች መረጃ የሚያገኙበት ቦታ፣

- GGG Migration

የጥገኝነት ሕግ እንዲሁም ስለ የውጭ ዜጋዎች ሕግ በሚመለከት መረጃ የሚያገኙበት ቦታ፣

- Beratungsstelle für Asylsuchende BAS
- Freiplatzaktion

የጀርመንኛ ቋናቋ መናገር አይችሉም? ካልቻሉ ሊያስተረጉምሎት የሚችል ሰው ይዘው መሄድ ይችላሉ። አለበለዚያም ተርጓሚ እንዲመደብሎት መጠየቅ ይችላሉ።

## ተጨማሪ መረጃ ሊንኮች፣ አድራሻዎች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ማብራሪያ ጽሑፎች

www.hallo-baselstadt.ch/am/sprache-und-integration/integration

# ለመወሃሃድ የሚረዱ አቅርቦቶች

በት/ቤት፣ በሙያ ስልጠና እና በስራ ቦታ ከሁሉም በተሻለ ሁኔታ መወሃሃድ ይችላሉ። ምናልባትም ስራ አይኖሮት ይሆናል ወይም የሙያ ስልጠና ላይ ላይሆኑ ይችላሉ። እንዲሁም ትምህርት ላይ ላይሆኑ ይችላሉ። ይህ ከሆነ ለመወሃሃድ የሚያግዙ የተለያዩ አቅርቦቶችን መጠቀም ይችላሉ።

## ልዩ አቅርቦቶች

በተለይ አዲስ ወደ ባዝል ለመኖር ለመጡ ሰዎች የሚሆኑ ብዙ አቅርቦቶች አሉ። ለምሳሌ ይህል፣ በጠርጴዛ ዙርያ መነጋገር፣ የእረፍት ግዜ አቅርቦቶች፣ ሴሚናሮች ወይም ኮርሶች ይጠቀሳሉ። እነዚህ አቅርቦቶች ቶሎ እንዲለምዱ እና አዲስ ሰዎችን መተዋወቅ እንዲችሉ እንዲረዳዎት የታሰቡ ናቸው። የ"GGG Migration" ምክር አገልግሎት ጽ/ቤት ስላሉት አቅርቦቶች መረጃ ይሰጣል።
በካንቶኑና በመኖሪያ ሰፈርዎ አዲስ ነዋሪዎችን ለመቀበል ዝግጅቶችን ያካሂዳሉ። እዛም ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎችን እና ለመጀመሪያ ያክል የሚሆን አጠቃላይ ዕይታ እንዲኖሮት ያስችሎታል።

## ማህበራት

ብዙ ስዊዘርላንዳውያን የማህበር አባላት ናቸው። የተለያየ ፍላጎት ላላቸው እንደፍላጎታቸው የተለያዩ ማህበራት (Verein) አሉ። ለምሳሌ ያህል የስፖርት ክለብ ማህበራት ወይም ባህላዊ ማህበራት፣ የአንድ ማህበር አባል መሆን አዲስ ሰዎችን ለመተዋወቅ ያስችላል። ብዙዎቹ ማህበራት ለሁሉም ሰው ክፍት ናቸው።

## የስደተኞች ድርጅቶች

የስደተኞችም ማህበራት አሉ። የማበራቱ አባላት አብዛኛውን ግዜ ተመሳሳይ ቋንቋ ይናገራሉ፣ ከአንድ አገር ነው የመጡት ወይም ተመሳሳይ ሃይማኖት አላቸው። እነዚህ ማህበራት ለስዊዘርላንድ እና ለባዝል ከተማ ካንቶን አዲስ መጤዎች ብዙውን ግዜ አቅርቦት አላቸው። የመዋሃድ ሂደቱ እንዲሳካ አስተዋጽኦና ድጋፍ ያደርጋሉ።

## አቅርቦቶች ለወጣቶች

ወጣቶች በትርፍ ጊዚያቸው ያሉትን አቅርቦቶች ቢጠቀሙ፣ ከሌሎች ከእድሜያቸው ጋር ተመጣጣኝ ከሆኑ ወጣቶች ጋር እንዲተዋወቁ ያስችላቸዋል። ፕሮጀክት ላይ መሳተፍና የራሳቸውን የግላቸውን ሃሳብ ማቅረብ ይችላሉ። ባለሙያዎች ወጣቶችን የሙያ ድጋፍ እንዲሁም አብረዋቸው በመሆን ሙያዊ ክትትል ያደርጉላቸዋል (Jugendarbeit)። በመሰረቱ አቅርቦቶቹ ከክፍያ ነጻ ናቸው።

## የአካባቢ የመገናኛ ማዕከላት

የአካባቢ የመገናኛ ማዕከላት (Quartiertreffpunkte) ለሁሉም ሰው ክፍት ናቸው። ለቤተሰቦች፣ ለአረጋውያን እና ትንሽ ጀርመንኛ ለሚናገሩ ሰዎች ጭምር የሚሆኑ አቅርቦቶች አላቸው። አንዳንድ የመገናኛ መዝናኛ ማዕከላት የቤተሰብ ማዕከሎች ናቸው። የአካባቢ የመገናኛ ማዕከላት የዕለት ተዕለት ሕይወትን በሚመለከት ምክርና ድጋፍ ይሰጣሉ። በመገናኛ መዝናኛ ማዕከላት ቤተሰባዊ በዓሎችን እና ሌላ ልዩ ዝግጅቶች ለማክበር ክፍሎችን መከራየት ይቻላል።

## ተጨማሪ መረጃ ሊንኮች፣ አድራሻዎች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ማብራሪያ ጽሑፎች

www.hallo-baselstadt.ch/am/sprache-und-integration/integrationsangebote

# ቋንቋ

ለBasel-Stadt አዲስ ነዎት እና እስካሁን ድረስ ጀርመንኛ መናገር አይችሉም? በተቻሎት መጠን ቀልጥፈው ጀርመንኛ መማር አለብዎት። ቋንቋውን የሚናገሩ ከሆነ አገሪቷን እና ህዝቡን የበለጠ ማወቅ ይችላሉ። በቀላሉ ስራ እንዲያገኙ ይረዳዎታል።

## መደበኛ ጀርመን ቋንቋ / የስዊዘርላንድ ጀርመንኛ (DE)

ስዊዘርላንድ አራት ብሄራዊ ቋንቋዎች አሏት፣ ጀርመንኛ፣ ፈረንሳይኛ፣ ጣልያንኛ እና ሮማንሽ ናቸው። የBasel-Stadt ካንቶን ኦፊሲያላዊ ቋንቋ ጀርመንኛ ነው። መደበኛ ጀርመንኛ እና የስዊዘርላንድ ጀርመንኛና ተብለው ይከፈላሉ።

- መደበኛ የጀርመን ቋንቋ (Standarddeutsch)
  ጀርመንኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች የሆኑ ስዊዘርላንዶች በመደበኛ ጀርመን ቋንቋ ነው የሚጽፉት። ት/ቤትም እና አልፎ አልፎም በራዲዮና በቴለቭዥንም ጭምር የሚናገሩት በመደበኛ ጀርመን ቋንቋ ነው፣

- የስዊዘርላንድ ጀርመንኛና (Schweizerdeutsch)
  የስዊዘርላንድ ጀርመንኛና የጀርመን ቋንቋ ዲያሌክት ነው። ምንም እንኳን ጥሩ ጀርመንኛ መናገር ቢችሉም፣ ምናልባት የስዊዘርላንድ ጀርመንኛና ቋንቋ ለመረዳት ይከብዶት ይሆናል። ጥቂት እንኳን አይረዳዎትም? የማይረዳዎት ከሆነ ከእርሶ ጋር በመደበኛ የጀርመን ቋንቋ እንዲናገሩ መጠየቅ ይችላሉ። የግድ የስዊዘርላንድ ጀርመንኛና ቋንቋ እንዲናገሩ አይጠበቅብዎትም። ቢሆንም ግን ከተወሰነ ግዜ በኋላ ቢችሉና ቢረዳዎት መልካም ነው።

## ጀርመን እና ልጆች (DE)

ልጅዎ ከጀርመን ቋንቋ ውጪ የሌላ ቋንቋ ተናጋሪ ነው? ከሆነ ጀርመንኛ ቋንቋ ተናጋሪ ከሆኑ ልጆች ጋር ቀልጥፎ ቢተዋወቅ ጥሩ ነው። ይህም ልጅዎ ቋንቋ የሚማርበት ፈጣኑ መንገድ ነው። ለምሳሌ ያህል ከልጆች የጨዋታ ግሩፕ ጋር መደባለቅ አለበት። ለወላጆች እና ለልጆችም ጭምር የተመቻቸ ልዩ አቅርቦት አለ። ልጅዎ እሰከ አሁን ድረስ ጀርመንኛ መናገር አይችልም ወይም ጥቂት ብቻ ነው የሚችለው? ይህ ከሆነ መዋዕለ ሕጻናት ከመግባቱ ቢዘገይ ከ1 ዓመት በፊት ጀርመንኛ መማር አለብት። ይህንንም በሚመለከት መዋዕለ ሕጻናት ከመጀመሩ ከ18 ወራት በፊት አስቀድመን በደብዳቤ እናስታውቆታለን። ለምሳሌ ያህል ይህ አቅርቦት የሚከተሉትን ይጨምራል፣

- የጨዋታ ግሩፕ፣ በጀርመንኛ ድጋፍ ያለው
- የልጆች የቀን እንክብካቤ ማዕከል (Kita)፣ ጀርመንኛ ቋንቋ የሚነገርበት
- የቤተሰብ የቀን እንክብካቤ

እርሶም በልጅዎ የቋንቋ ዕድገት ላይ አስተዋጽዎና ድጋፍ ማድረግ ይችላሉ። ከልጅዎ ጋር ብዙ ይነጋገሩ፣ ልጅዎንም ያዳምጡት እንዲሁም ታሪኮችን ይንገሩት። በሚናገሩበት ግዜም በደንብ አቀላጥፈው በሚችሉት ቋንቋ ይነጋገሩ።

## የጽሑፍ ትርጉሞች / የቃል ትርጉም አገልግሎት

ለባዝል አዲስ ነዎት እና እስካሁን ድረስ ጀርመንኛ መናገር አይችሉም? ካልቻሉ አንዳንድ ግዜ እንደአስፈላጊነቱ ተርጓሚ ያስፈልጎታል። ምናልባት ዘመዶችዎን ወይም ወዳጆችዎን መጠየቅ ይችላሉ። ይሁን እንጂ አንዳንድ ንግግሮች ለመረዳት አስቸጋሪ ወይም በጣም ግላዊ ናቸው። ለምሳሌ የሆስፒታል ወይም የአስተዳደር ጽሕፈት ቤት ቀጠሮ ሊሆን ይችላል። በባህሎች መካከል ዕውቀት ያለው ተርጓሚ ያስፈልጎት ይሆናል። እነዚህ ባለሙያዎች በተለይ ከሌላ ባህል ለመጡ ሰዎች፣ ማለትም እነዚህ ባለሙያዎች ባህልዎን ያውቃሉ እና እንዲሁም ሁሉንም መረዳት እንዲችሉ አድርገው መተርጎም ይችላሉ።
ከአስተዳደር ጽሕፈት ቤቶች ደብዳቤ ተልኮሎት እና ይዘቱንም አልተረዱትም? ወይም ቅጽ መሙላት አለብዎት ወይም ደብዳቤ መጻፍ ይፈልጋሉ? ይህንን በሚመለከት እዚህ እርዳታ ያገኛሉ፣

- GGG-Migration የትርጉም አገልግሎት ጽ/ቤት

## የቋንቋ ችሎታ ደረጃዎች በውጭ ዜጎች ሕግ- እና በሲቪል ሕግ (DE)

ምናልባት „የመቆያ ፍቃድ B“ Aufenthaltsbewilligung (B) ወይም „የመኖሪያ ፈቃድ C“: Niederlassungsbewilligung (C) ማመልከት ይፈልጉ ይሆናል። ወይም ዜጋ መሆን ይፈልጉ ይሆናል። ጀርመንኛ የመጀመሪያ የአፍ መፍቻ ቋንቋዎ አይደለም? ካልሆነ በቂ የጀርመንኛ ችሎታ ያሎት መሆኑን ማረጋገጫ ያስፈልጎታል።
ለማመልከትም የሚያስፈልጎትን ሙሉ መረጃዎች እዚህ ያገኛሉ፣

- የስደተኞች አስተዳደር ጽ/ቤት (Migrationsamt)

## ተጨማሪ መረጃ ሊንኮች፣ አድራሻዎች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ማብራሪያ ጽሑፎች

www.hallo-baselstadt.ch/am/sprache-und-integration/sprache

# ጀርመንኛ ቋንቋ መማር

በጀርመን ኮርስ ጀርመንኛ ቋንቋ በደንብ መማር ትችላለህ። ብዙ የተለያዩ ዓይነት የጀርመንኛ ቋንቋ ኮርሶች አሉ።

## አቅርቦቶች

ብዙ የተለያዩ ዓይነት የጀርመንኛ ቋንቋ ኮርሶች አሉ። ለምሳሌ፣

- ትናንሽ ልጆች ካለዎት የህጻናት እንክብካቤ ያለበት ኮርስ ይመዝገቡ።
- ምናልባት የላቲን /የእንግሊዝኛ/ ፊደል ዕውቀት ከሌለዎት ወይም ማንበብና መጻፍ ችግር ካለብዎት፣ የማይምነት/የፊደል ትምህርት/ ኮርስ (Alphabetisierungskurs) ይመዝገቡ።.

ምን ዓይነት ኮርሶች እንዳሉ ለማወቅና እና ኮርሶቹ ምን ያህል እንደሚያስከፍሉ መረጃ ለማግኘት እዚህ ይጠይቁ።

- የጎልማሶች ትምህርት ሙያዊ ቢሮ (Fachstelle Erwachsenenbildung)
- GGG Migration

## የቋንቋ ችሎታ ደረጃ

አንድ ሰው ምን ያህል ጀርመንኛ መናገር እንደሚችል (Gemeinsamen Europäischen Referenzrahmen) „በጋራ የአውሮፓ የማጣቀሻ ማዕቀፍ“ መገምገም ይቻላል። ይህም በምህጻረ ቃል GER ተብሎ ይጠራል። GER የቋንቋ ደረጃ መገምገሚያ መለኪያ ነው። 6 ደረጃዎችም አሉት። እነሱም፣ ኤ1፣ ኤ2፣ ቢ1፣ ቢ2፣ ሴ1 እና ሴ2.ናቸው። ኤ1 ወይም ኤ2.ደረጃ ላይ ከደረሱ፣ መሰረታዊ የጀርመን የቋንቋ ዕውቀት አለዎት ማለት ነው። ሴ1 እና ሴ2.ደረጃ ላይ ከደረሱ፣ ከፍ ያለ የቋንቋ ደረጃ ላይ ደርሰዋል ማለት ነው።

- ስዊዘርላንድ ውስጥ ተቀባይነት ያለው የሙያ ስልጠና ማድረግ ከፈለጉ፣ ቤ1 ወይም ቤ2 የቋንቋ ደረጃ ያስፈልጋል።
- ዩንቨርስቲ መማር ከፈለጉ፣ ሴ1 ወይም ሴ2.የቋንቋ ደረጃ ያስፈልጋል።

## ፋይናንስ ማድረግ

ለባዝል ከተማ አዲስ ነህ፣ እንዲሁም „የመቆያ ፍቃድ B“ Aufenthaltsbewilligung (B) ተሰጥቶታል? ተሰጥቶት ከሆነ በተጨማሪ የጀርመን ኮርስ ለመመዝገብ የሚያስችል Gutschein ኩፖን ይሰጥዎታል። ይህ ኩፖን 80 የትምህርት ጊዜዎችን በነጻ እንድትማር ያስችልሃል። በካንቶኑ ዕውቅና በተሰጠው የቋንቋ ት/ቤት ኩፖኑን በመስጠት መመዝገብ ይቻላል። ይህ ኩፖን ከገቡበት ግዜ ጀምሮ እስከ 12 ወራት ድረስ ያገለግላል። ከዚያ በኋላ ተጨማሪ የጀርመንኛ ኮርስ መማር ይፈልጋሉ? መቀጠል ከፈለጉ ለቀጣዩ ትምህርት ክፍያ መክፈል አለብዎት። የኮርሶቹ የክፍያ ዋጋ የተለያየ ነው። በተቻለ መጠን ዋጋ ቢያነጻጽሩ ይመረጣል። የKanton Basel-Stadt ለአንዳንድ ኮርሶች የገንዘብ ድጋፍ ያደርጋል። በዚህም ምክንያት ለነዚህ ኮርሶች አነስተኛ ገንዘብ ይከፍላሉ።

## ተጨማሪ መረጃ ሊንኮች፣ አድራሻዎች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ማብራሪያ ጽሑፎች

www.hallo-baselstadt.ch/am/sprache-und-integration/deutsch-lernen